
# በጆይስ ማየር

ከግራ መጋባት ህይወት የመውጫው መንገድ



# ለምን ጌታ ሆይ?

# ለምን ጌታ ሆይ?

# ለምን ጌታ ሆይ?

## ከግራ መጋባት ህይወት የመውጫው መንገድ

በጆይስ ማየር

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ ያለ አሳታሚው ፈቃድ በማንኛውም መንገድ ማሳተም በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ በማንኛውም  መልኩ መጽሃፎቹን መውሰድ ከተፈለገ ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ በግርጌ ማስታወሻ ሊመላከት ይገባዋል ፡፡

copy right @ 1995 by Joyce Meyer

ከጆይስ ማየር አገልግሎት በነፃ የሚታደል

አዘጋጅና አከፋፋይ

ሮይ ፊልም ፕሮዳክሽን

ስ.ቁ  251- 961-125646
251-961-125647

2008

አዲስ አበባ

ኢተዮጵያ

# ማውጫ

መቅድም

1 የግራ መጋባት ምክንያቶች 1

2 ከምክንያት ደርዳሪነት ነጻ መውጣት 6

3 የእምነት አስተሳሰብ 9

4 ለቀኑ ብቻ 12

5 ቢሆን ኖሮ 17

6 እንደዛቢሆንስ? 21

7 በጭንቅላት አትምሩ 26

8 ‹‹ምክንያት ደርዳሪነት›› መታለልን ይፈጥራል 32

9 ግራ መጋባት ደስታን ይነጥቃል 38

# መቅድም

በዮሐንስ የወንጌል መፅሐፍ 10፡10 ላይ «ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ» ይላል፡፡

እግዚአብሔር አምላክ የሰጠንን የደስታ ህይወት እንዳንኖር በዛው መጠን ሰይጣን ደስታችንን ሊነጥቀን አብዝቶ ይተጋል። በዚህ መጽሐፍ አማካኝነት እንዲህ ያለውን የሰይጣንን ተግዳሮት አሸንፋችሁ «እግዚአብሔር እርሱ እግዚአብሔር ነው» በሚል ጽኑ መንፈስ መመላለስ ትችሉ ዘንድ የሁልጊዜ ፀሎቴ ነው፡፡ ወደዚህ መረዳት ውስጥ ስትገቡ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል መስዋእቱ ያመጣላችሁን የደስታና የሠላም ህይወት በሙላትመኖር ትጀምራላችሁ፡፡

# 1

## የግራ መጋባት ምክንያቶች

ግራ ተጋብታችኋል? አንድ እንግዳ ነገር፣ ፈጽሞ ሊገባችሁ ያልቻለ ጉዳይ በህይወታችሁ ሳትፈልጉት እየሆነባችሁ ይሆን? ምናልባት የነገሩ ምክንያት ከዚህ ቀደም በአንድ የህይወት አጋጣሚያችሁ ውስጥ ሳይገባችሁ ያለፈ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ የተነሳ «ጌታ ሆይ ምነው  እንዲህ ያሉ ነገሮች በእኔ ላይ ?  … ምነው እንዲህና  እንዲያ ሆነው ቢያልፉ ኖሮ? አባት ሆይ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በእኔ ህይወት ውስጥ ለምን እንዳለፉ ሚስጠሩ አልገባኝም » እያላችሁ ትናገሩ ይሆናል፡፡

ልዩ ልዩ ግራ መጋባቶች በብዙ ሠዎች ህይወት ውስጥ እንደሚያልፉ ማስተዋል ከጀመርሁ ቆይቻለሁ፡፡ እኔም ከዚህ በፊት እንዲህ ባለው ግራ የመጋባት ህይወት ውስጥ ማለፌን አስታውሳለሁ፡፡ ያም ብቻ አይደለም ግራ መጋባት በሌሎች ሠዎች ላይም የሚያደርሰውን ከፍተኛ ስቃይ በሚገባ አውቀዋለሁ፡፡ከዚህ የተነሳ ሠዎች ግራ ከመጋባት ህይወት ውስጥ የሚወጡበትንና ደግሞ ግራ መጋባት እንዴት መከላከል እንደሚችሉ ደጋግሞ አስቤበታለሁ፡፡

በአንድ ወቅት ካንሳስ ከተማ ውስጥ በአንድ ሥፍራ ስብሰባ አድርጌ ነበር፡፡ በዛ ስብሰባ ላይ ቁጥራቸው ቢያንስ 300 የሚሆኑ ሠዎች ተሰብስበው ነበር፡፡

ንግግር እያደረግሁ ሳለ በመካከል በአንዳንድ ጉዳዮች ምክንያት ግራ የተጋቡ ሠዎች ካሉ እጃቸውን እንዲያነሱ ጥያቄ አቀርብኩላቸው፡፡

የሚገርመው ነገር ከተሰብሳቢዎቹ መካከል እጃቸውን ለጥያቄዬ ያላነሱት በቁጥር 2 ሠዎች ብቻ ሆነው ተገኙ፡፡ ከሁለቱ ሠዎች መካከል የራሴው ውድ ባለቤት ነበር፡፡

ይገርማል! አሁንም አጽንኦት ለመስጠት ከተሰበሰቡት 300 ሠዎች መካከል 298 ሠዎች ግራ በመጋባት ህይወት ውስጥ ነበሩ! የዚህን አሃዝ ቁጥር ወደ መቶኛ ስንለውጠው 99.3 % ይደርሳል ማለት ነው፡፡

ይህ አስደንጋጭ የግራ መጋባት አሃዝ በአንድ ሥፍራ ዝም ብዬ እንድቀመጥ አላደረገኝም፡፡ ሌሎችንም ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በተለያዩ ሥፍራዎች አነስተኛ ጥናቴን ማድረጌን ገፋሁበት፡፡ የሚገርመው ነገር ውጤቱ ይለያይ እንጂ በሁሉም ሥፍራዎች ግራ የተጋቡ ሠዎች ቁጥር ከፍተኛ ሆኖ አግኝቼዋለው፡፡

ወገኖቼ ጉዳዩ እረፍት ሊሰጠኝ አልቻለም፡፡ አንድ መፍትሔ መገኘት እንዳለበት ደጋግሜ አሰብሁ፡፡ በጌታ ፊት በፀሎት መንፈስ ሆኜ ምክንያቱን እንዲነግረኝ ጠየቅሁት፡፡

እርሱም «የምታገለጊያቸውን ሠዎች ስለምንም ነገር በሀሳባቸው ማውጣትና ማውረድ እንዲያቆሙ ንገሪያቸው፤ ያን ጊዜ ግራ ከመጋባት ህይወት ውስጥ ፈጥነው ይወጣሉ» ሲል መለሰልኝ፡፡ ክብር ለእርሱ ይሁን! ይህ የጌታዬ ቃል በእኔም ህይወት ፈጥኖ ለውጥ ማምጣት ጀመረ፡፡

ይገርማችኋል! አሁንም እልቁ መሳፍርት የሌላቸው ጥያቄዎች በየጊዜው በልቤ ውስጥ አልፎ አልፎ መፈጠራቸው አልቀረም፡፡ ይሁን እንጂ ትኩረቴን አብዝቼ ወደ እነርሱ አላደርግም፡፡

አሁንም ክብር ሁሉ ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ይሁን! ሀሳቦቼን ከማውጣትና ከማውረድ ማንነት ገላግሎኛል፡፡ ትኩረቴን በተከማቹ ሀሳቦቼ ላይ እንዳላውል ፀጋውን አብዝቶልኛል፡፡ ለሀሳቦቼ ምክንያት እየደረደርሁ ግራ መጋባት ውስጥ እንዳልከርም ምህረቱን አግንኖልኛል፡፡ ይልቁንም ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሠዎች በመልእክቱ ያሰፈረው ቃል ልቤን ይገዛኛል፡፡

"*የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን።*" (2ኛ ቆሮ 10፡5)

ግራ መጋባትን አስመልክቶ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣው መርህ ቀላል ነው! አይደለም ወገኖቼ? ሁልጊዜ ወደ እኛ ለሚመጡት የሀሳብ ክምችቶች ምክንያት አለመደርደር ከግራ መጋባት ህይወት ፈጽመን እንድንወጣ ትልቅ እገዛ ያደርግልናል፡፡

እኛና ሰይጣን ጦርነት የምንገባበት ምቹ ሥፍራ አይምሯችን እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ በአይምሯችን ውስጥ ሰይጣንን እሸንፋለን ወይም እንሸነፋለን፡፡

ሰይጣን በግራ መጋባት እንድንሸነፍ ሁልጊዜ አብዝቶ ይተጋል፡፡ የግራ መጋባት ምንጩ እርሱ ነውና፡፡ አምላካችን እግዚአብሔር ግን የሰላማችን ምንጭ ነው፡፡

ሐዋሪያው ጳውሎስ «እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና» ብሎ እንደተናገረ (1ኛ ቆሮ 14፡33)

ሐዋሪያው ጳውሎስ በሌላም ሥፍራ ለሀሳቦቻችን ምክንያቶችን መደርደር አቁመን እግዚአብሔር የሰጠንን ሰላም በሙላት አጣጥመን ብቻ እንድንኖር እንዲህ ሲል ያሳስበናል፡-

"የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን።"(2ኛ ቆሮ 10 4-5)

ቃሉ ከላይ እንደሚነግረን ሰይጣን የሀሳብ ጦርነት የሚከፍትብን አይምሯችን ውስጥ ነው፡፡ በአጭር ቃል አይምሯችን የጦርነት ቀጠና ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ወገኖቼ የእግዚአብሔር ቃል ከሀሳቦቻችን ጋር ትግል ውስጥ እንዳንገባ ከነገረን፣ ሌላ ምንም አማራጭ የለንም፡፡

የእግዚአብሔር ቃል ትዕዛዙ ብርቱ ነውና፡፡ ስለዚህ ትዕዛዙን ለመተግበር ወደ ኋላ አንልም፤ እንታዘዘዋለን እንጂ! በትዕዛዙ አማካኝነት ከገጠመን ግራ የመጋባት ህይወት ፈጥነን እንወጣበታለን! ለሀሳቦቻችን ምክንያት ለመደርደር ትግል ሲገጥመን ሀሳቦቻችንን ለክርስቶስ ሀሳብ እንዲገዙ ማድረግ ትልቅ መንፈሳዊ ጥበብ ነው፡፡

ከላይ ያነበብነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሰይጣን በእኛ ላይ ለሚከፍተው ጦርነት መሳሪያው ሀሳብ እንደሆነ አይተናል፡፡ እውነት ያልሆኑ ወይም የማይጨበጡ ሀሳቦችን በአይምሯችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ? ወይም ትክክል ያልሆኑ ምስለ ሀሳቦችን በአይምሯችሁ ላይ ተቀምጠው ስለ እነርሱ አሰላስላችሁ ታውቃላችሁ?

ለእነዚህ ሁሉ ሀሳቦች ምላሾችን ለመስጠት ሁላችንም በተፈጥሮአዊ የምክንያት ድርደራ ጥበቦቻችን ምላሽ ለመስጠት እንሞክራለን፡፡ የሚገርመው ነገር ምላሹ የሚገኘው በራሳችን ጥበብ ወይም ብልሃት ውስጥ አይደለም፡፡ ወገኖቼ አስቸጋሪ ለሆኑ ጥያቄቻችን መልሱ የሚገኘው አምላካችን እግዚአብሔር ጋር ብቻ ነው፡፡

በዚህ ምእራፍ ውስጥ አስቸጋሪ ለሆኑ አይምሯዊ ጥያቄዎቻችን የምናደርገው መፍጨርጨር የግራ መጋባት ምክንያት እንደሆነ አይተናል።

የጥያቄዎቻችንም መልስ የሚገኘው እግዚአብሔር አምላካችን ጋር ብቻ እንደሆነም ተረድተናል፡፡

ይሁን እንጂ በአንዳንድ ምክንያት እግዚአብሔር ለሁሉም ጥያቄዎቻችን መልስ ቢኖረውም ለእኛ ግን መልሱን ላይነግረን ይችላል፡፡ ወገኖቼ በዚህ መረዳት ውስጥ ሆነን አሁኑኑ የማይመለሱ ጥያቄዎቻችንንም ሳይቀር ለአምላካችን ለእግዚአብሔር እናስረክበው!

# 2

## ከምክንያት ደርዳሪነት ነጻ መውጣት

ከምክንያት ደርዳሪነት ህይወት ነጻ በመውጣቴ ምክንያት መደነቅ ውስጥ ሳትገቡ አስቀድማችሁ የእኔን የቀደመ ማንነት ልታውቁ ይገባል ብዬ አስባለሁ፡፡

ዱሮ ወጣት እያለሁ «የማንም ጉዳይ አይመለከተኝም፤ ስለማንም ጉዳይ አያሳስበኝም፤ በማንም ላይ አልደገፍም ይልቁንም የሚያዋጣኝ ነገር ቢኖር ለራሴ ጉዳይ ብቻ ትኩረት መስጠት ነው» የሚል የግል ፍልስፍና ነበረኝ፡፡ ጥቂት ድጋፍ ከሰዎች ዘንድ ቢያስፈልገኝ እንኳን በዛው መጠን ከሠዎች ብዙ መራቅ አዋጪ ነው ብዬ አስብ ነበር፡፡ እንዲህ ወዳለው ድምዳሜ የደረስኩት ሠዎችን በመቅረብ ከሚመጣው የስሜት መጎዳት ለማምለጥ ይረዳል ከሚል የግል እምነቴ የተነሳ ነበር፡፡

በግል ዛቢያ ላይ ብቻ ያሽከረከረኝ የነበረው የህይወት ልምምዴ በመጨረሻ እንደማያዋጣኝ ተረዳሁ፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ተግባር ለመምጣት ብዙ ጊዜ ፈጅቶብኛል፡፡ ከዚህ የተነሳ ብዙ ዘመኔን ስጨነቅ፣ ለልዩ ልዩ ሀሳቦቼ ምክንያት ስደረድር፣ ሳወጣ ሳወርድ፣ በልቦናዬም ሳሰላስል ከበድ ባለ ግራ የመጋባትና የጭንቀት ህይወት ውስጥ አልፊያለሁ፡፡ ራሴን በራሴ ነጻ አውጥቼ ለመኖር በጣርኩኝ ቁጥር በዛው መጠን በእግዚአብሔርና በሰዎች ላይ ያለኝ መተማመን እየጠፋብኝ መጣ፡፡

ታውቃላችሁ እግዚአብሔር በራሳችሁ ላይ ሳይሆን በእርሱ ላይ ብቻ እምነታችሁን እንድትጥሉ ይፈልጋል፡፡ የምትረዱትንም ሆነ የማትረዱትን ማንኛውንም ጉዳይ በጌታ ኢየሱስ ላይ በጣላችሁ ቁጥር በዛው መጠን ግራ የሚያጋቧችሁ ሀሳቦች በሙሉ ከእርሱ ዘንድ ምላሽ ያገኛሉ፡፡ በትክክለኛውም ጊዜ ተመለሰው በመገለጥ መንፈስ ወደ እናንተ ይመጣሉ፡፡

ሀሳብን በልብ ላይ አጭቆ በፀጥታ መኖር ትህትናን አያመለክትም። በዚህ ጉዳይ ላይ ቸልተኞች መሆን አይገባንም፡፡ ይልቁንም ያሳሰበበን ጉዳይ በሚገባ ሊረዳልን ለሚችለው አምላካችን አሳልፈን መስጠት አለብን፡፡

በእናንተ ወይም በወዳጃችሁ ልብ ላይ የከበደ አንዳች ጉዳይ ቢኖር ይልቁንም ሀሳባችሁ ወደ መፍትሔ ይመጣ ዘንድ ከአምላካችሁ ጋር በፀሎት መንፈስ ጉዳያችሁን ጀምሩ፡፡ መገለጥን አምጥቶ መፍትሔ እስኪያመጣላችሁ ድረስ መንፈስ ቅዱስ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ መረዳት እንዲሰጣችሁና እንዲያስተምራችሁ ጠይቁት፡፡ በእርግጥም ጊዜው በደረሰ ሠዓት የመረዳቱን መንፈስ አብዝቶ በእናንተ ላይ ያደርጋል!

አንድ የማይካድ እውነት ቢኖር አይህምሯችን ውስጥ በሆነ አጋጣሚ አንዳችን ጥያቄ መፈጠሩ አይቀርም፡፡ እኛም ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት መሞከራችን አይቀርም፡፡ ጥያቄው ካልተመለሰ ግን በልባችን ውስጥ ግራ መጋባትና መጨነቅ መፈጥሩ አይቀሬ ነው፡፡

ዳሩ ግን እንዲህ ካለው ህይወት ፈጥኖ ለመውጣት ከአምላካችን ዘንድ ምላሽ እንዳለን አምነን ለእርሱ ብቻ የሚገባውን ምስጋና መስጠት ይገባናል፡፡ እርሱም ነገርን በጊዜው ውብ አድርጎ ለጥያቄዎቻችን ፈጣን ምላሽ ይሰጠናል፡፡

ይህንን ልብ በሉ! በእኔ አጠራር የእምነት አስተሳሰብ ብዬ የምገልጸው እሳቤ አለ፡፡ በህይወታችን ከበውን ያሉትን ልዩ ልዩ ሀሳቦችና ግራ መጋባቶችን የምናሸንፈው በእምነት አስተሳሰባችን ነው፡፡ ይህንን የእምነት አቋም እሳቤን የራሳችን አድርገን ካልወሰድነውና ካልኖርበት በስተቀር ግራ መጋባትን የሚፈጥሩ ሀሳቦቻችንን ልናሸንፋቸው አይቻለንም፡፡ በሚቀጥለው ምእራፍ ጥቂት ስለ እምነት አስተሳሰብ ትንታኔ ለመስጠት እሞክራለሁ፡፡

# 3

## የእምነት አስተሳሰብ

ምናልባት እምነትን እንደ አስገዳጅ ሃይማኖት ቀነኖ ወይም ከእግዚአብሔር አለም አንዳች ነገር የምንቀበልበት መንገድ አድርገን እንቆጥረው ይሆናል፡፡ በኤፌሶን 2፡8-9 ላይ ግን «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም» የሚል ቃል እናገኛለን። በዕብራውያን 11፡1 ላይ ደግሞ «እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው» የሚል ስለ እምነት ማብራሪያ የሚሰጥ ቃል እናገኛለን፡፡ ከዚህም ባሻገር እምነትን በተለያዩ መንገዶች የትርጉም አቅጣጫውን ማሳየት እንችላለን፡፡ ይሁን እንጂ እምነትን እጅግ ቀለል ባለ የትርጉም አንድምታ ይገባን ዘንድ «እምነት አስተሳሰብ አለው» ብለን ብያኔውን መጀመር እንችላለን፡፡

የእምነት አስተሳሰብ አቅጣጫው ወደ እረፍት ይመራናል፡፡ በዕብራውያን 4፡3 ላይ «ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ምንም እንኳ ቢፈጸም እንዲህ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ እንዳለ፥ እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን» የሚል ቃል ተጽፎልናል፡፡ ከዚህ ቃል እንደምንረዳው ወደ እረፍት ህይወት ለመግባት የመጀመሪያው ግብዓት የሠው ልጅ ጥረትና ብዙ ተግባር ሳይሆን በእምነት ላይ የተመሰረተ መንፈሳዊ ማንነት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

በዚሁ የዕብራውያን ምእራፍ 4 ቁጥር 10 «ወደ ዕረፍቱ የገባ፥ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፥ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና» ተብሎ እንደተጻፈ ማለት ነው፡፡

የእምነት አስተሳስብ ሁልጊዜ ይህንን መርህ አንግቦ ይቆማል፡፡ የመርሁ ቃል በ1ኛ ጴጥሮስ 5፡7 ላይ «ወደ ዕረፍቱ የገባ፥ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፥ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና» ሲል በግልጽ ተቀምጦልናል፡፡

አንድ ሚስጥር ልንገራችሁ እግዚአብሔር ምን እየሰራ እንደሆነ ለማወቅ በአይህምሯዊ አስተሳሰብ ማውጣትና ማውረዳችሁን ትታችሁ ይልቁንም አብዛኛውን ጊዜያችሁን እርሱን ወደ ማወቅ ባለጠግነት ትደርሱና ትጋት ታሳዩ ዘንድ እመክራችኋለሁ።

የእምነት አስተሳሰብ ጭንቀትን አካትቶ አይጓዝም፤ ነገ ስለሚሆነው ጉዳይ ትካዜ ውስጥ ገብቶ እምብዛም በሀሳብ አይወጣጠርም፡፡

ዛሬ ላይ ቆሞ ነገን ማወቅ በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ ገብቶ እንኳን መጓዝ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የእምነት አስተሳሰብ በነገው ጉዞው ላይም ኢየሱስ እንዳለበት ያውቃልና፡፡ ምክንያቱም ኢየሱስ ያለና የነበረ፣ እንዲሁም ሊመጣያለ ጌታ ነውና፡፡ የፍጥረትን ታሪክ እንኳን ስናወሳ እርሱ የምድር መሠረት ከመጣሉ በፊት ነበር፡፡ ፍጥረት ግዑዝ ሆኖ ወደሚታየው አለም ሲመጣ በዛ ውስጥም ንቁ ተሳታፊ ነበር። ወገኖቼ ሆይ እናንተንም ከመፈጠራችሁ በፊት ያውቃችሁ ነበር፡፡ በእናታችሁ ማህፀን ውስጥ ሳላችሁ በድንቅ እጆቹ ያበጃጃችሁ እርሱ ነው፡፡

በዘመን ቁጥር ውስጥ እግዚአብሔር በጅማሬ ላይ ብቻ ነበር ብሎ መደምደም አይቻልም፡ ፡ እርሱ አልፋና ዖሜጋ ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እርሱ ብቻ ነው፡ ፡

በፍጻሜ ላይስ? በውኑ ኢየሱስ ከእኛ ጋር ነውን ? በስተመጨረሻ ላይ ጥሎን የሚሄድ ይመስላችኋልን ? በፍጹም በእኛ የጀመረውን ይጨርሰዋል እንጂ በአንድ የታሪክ አጋጣሚ መንገድ ላይ ጥሎን አይሄድም!

*የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ* (ዕብ 12፡2) ፡፡

በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና (ፊሊ 1፡6)

ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ፍጻሜው ድረስ ከእኛ ጋር ነው! እርሱ መጨረሻችን ወይም *ዖሜጋ*ችን ነው፡፡ እንዲህ ማለትን እወዳለሁ፤ «እርሱ ኢየሱስ አልፋና *ዖሜጋ* … መጀመሪያና መጨረሻ ብቻ አይደለም፡፡ እርሱ በአልፋና በ*ዖሜጋ* መካከልም ያለ በረከታችን ነው »፡፡

እስቲ ለጥቂት ጊዜ ኢየሱስ ከወደፊት ጉዟችን ቢዘገይስ ብላችሁ አስቡ! ለምሳሌ ዛሬ ላይ ቆሜ የምፈልጋቸው በርካታ ነገዎች አሉኝ። እናንተም የምትፈልጓቸው በርካታ ነገዎች አሉ፡፡

የሚገርም ነው! በእርግጥም ይገርማል! ነገዎቻችን በኢየሱስ እጅ ላይ እንደሆኑ ሳስብ ልቤ በሚያስደንቅ ሀሴት ይሞላል፡፡ አኔም ሆንኩኝ ነገዬ በአዳኜ መዳፍ ላይ በክብር ተቀምጠናል!

*እነሆ፥ እኔ በእጄ መዳፍ ቀርጬሻለሁ፥ ቅጥሮችሽም ሁልጊዜ በፊቴ አሉ* (ኢሣ 49፡16)

# 4

## ለቀኑ ብቻ

«ምክንያት ደርዳሪነት» ወይ ኋላ ይጎትተናል ወይም ወደፊት ያስፈነጥረናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል የሚናገረውን ቃል አስታውሱ፤ «እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው» (ዕብ 11፡1)፡፡ ይህ የዕብራውያን ምእራፍ ቃል የአሁን ጊዜን ያመለክታል፡፡ እምነትን ይዛችሁ በኃላፊ ጊዜ ለመኖር የምትሞክሩ ከሆነ ህይወት እጅግ አስቸጋሪ እንደምትሆንባችሁ በደምብ አስቡ፡፡ እንደዚሁም እምነትን ይዛችሁ ነገ ብቻ ስለሚሆነው ነገር ብቻ በሀሳባችሁ የምታወጡና የምታወርዱ ከሆነ ይህም ሌላው መንፈሳዊ ኪሳራ ነው፡፡ እምነት የትላንትና የነገ ብቻ ገፅታ አይደለም። ትክክለኛ እምነት ዛሬን በዛሬ ጊዜ መኖር ነው። ለዚህም ነው እግዚአብሔር አምላክ ለሙሴ «ያለና የሚኖር» እኔ ነኝ ሲል የተናገረው (ዘፀ 3፡14)፡፡ «ያለና» የሚለው ቃል የአሁን ጊዜን ያመለክታል፡፡ እምነትን በዚህ መልኩ ከተረዳን ህይወትን በመንገዳችን ሁሉ ቀና ሆና እናገኛታል።

በማቲዮስ ወንጌል 24፡27 ላይ በአንድ ወቅት ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በነበሩ ጊዜ «እኔ ነኝ» ብሏቸዋል፡፡ ይህ የጌታ ኢየሱስ ቃል የአሁን ጊዜን አመላካች ነው፤ «ወዲያውም ኢየሱስ ተናገራቸውና። አይዞአችሁ፥ እኔ ነኝ፤ አትፍሩ አላቸው» (ማቲ 27፡24)

በዚህ ከፍል ውስጥ ያለውን ቃል በደምብ አስተዋላችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ ነኝ» ያለው ለእናንተ የአሁን ጊዜ ጉዳይ ነው፡፡

ኢየሱስ በቃሉ «እኔ ነኝ» ካለ ወገኖቼ ሁሉም ነገር ሰላም ነው! ሁሉም ነገር በአሁኒቷ ሠዓት ደህና እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ስላለፈ ወይም ስለ ነገ ጉዳይ መጨነቅ በራሱ ዛሬያችንን ይሰርቅብናል።

ስለዚህ ወገኖቼ ሆይ በዛሬ ጊዜ ላይ ቆሞ «እኔ ነኝ» ያለውን ጌታ ታምናችሁ ከመጨነቅ ህይወት በፍጥነት እንድትወጡ አሳስባችኋለሁ! ምክንያቱም የምትኖሩበት ፀጋ የተሰጣችሁ ለዛሬ ነው፡፡

የትላንትናውን ፀጋ ተጠቅማችሁበታል፤ አሊያም አልፏል፤ የነገን ፀጋ ደግሞ የምትጠቀሙበት ገና ነገ ነው፡፡ ፀጋ ማለት አንድን ነገር በአሁን ጊዜ እንድናደርግበት የሚያስችለን መለኮታዊ ብቃት ነው፡፡ ማናቸውንም ነገር በሞገስና በኃይል እንድናከናውን የሚያስችለን የመንፈስ ቅዱስ ኢጋዥነት ነው፡፡

ፀጋን አንድ ሊመጣ ላለ ጊዜ የምናጠራቅመው አይደለም፡፡ ዛሬውኑ የምንጠቅምበት የእግዚአብሔር ደጋፊነት ነው እንጂ!

እስራኤላውያን በምድረ በዳ ውስጥ ሆነው ያሳለፉትን ህይወት ታስታውሱታላችሁ? እግዚአብሔር በሚያስገርም መለኮታዊ ባርኮት መናን ከሠማይ በየቀኑ ያዘንብላቸው ነበር፡፡ የሚገርመው ነገር ለእስራኤላውያን መና ከሠማይ በየዕለቱ እየዘነበላቸው ለነገ ደግሞ ስንቅ ይሆናቸው ዘንድ መናውን ማጠራቀም ፈልገው እንደነበር እናስታውሳለን፡፡

ምናልባት እግዚአብሔር የነገውን መና ርስቶት ላያዘንብልን ይችላል ብለው ይሆንን? በዚህ ዘመንም እኛም ይህንን የሚመስል ህይወት ውስጥ እንገኛለን፡፡ ዛሬ እግዚአብሔር የምንኖርበትን ፀጋ ሰጥቶን ሳለ ነገ የምንኖርበት ፀጋ ለማግኘት አብዝተን እንጨነቃለን።

የሚገርመው ነገር እግዚአብሔር እስራኤላውያኑ የዛሬያቸውን እንጂ የነጋቸውን መና እንዳይሰበስቡ በጥብቅ አሳስቧቸው ነበር (ከሰንበት ቀን በስተቀር)፡፡ የሚገርመው ነገር ነጋቸውን አስበው ዛሬ ላይ መና የሰበሰቡ ሦዎች ኪሳራ ውስጥ ወድቀዋል፡፡ ለነጋቸው ያሳደሩት የዛሬ መና እንደበሰበሰባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡

ወገኖቼ ከላይ ያየነውን የእግዚአብሔርን ቃል በማስተዋል በእናንተም ህይወት ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን አሳስባችኋለሁ፡፡ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ውስጥ እያሉ የገጠማቸው የመና ታሪክ ዛሬም ለእኛ ህይወት ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል ብዬ አምናለሁ፡፡ አንድ ጥያቄ እስቲ ልጠይቃችሁ፡፡

ዛሬ ላይ ቆማችሁ ለነገ የምትጨነቁት፣ ልዩ ልዩ ሀሳቦችንም በአይህምሯችሁ ውስጥ የምታወጡትና የምታወርዱት የነገውን መናችሁን እያሰባችሁ ይሆን? በሦማይ የሚኖረው አምላካችሁ የነጋችሁን ጉዳይ ለእርሱ እጅ አሳልፋችሁ እንድትሰጡት ይፈልጋል፡፡

በምሳሌ 3፡5 ላይ «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ» የሚል ቃል እናገኛለን፡፡ ይህ ቃል ዛሬውኑ በህይወታችን ውስጥ ነፍስ ዘርቶ ይቁም!

በአንድ ወቅት አንድ መጽሐፍ ላይ ያነበብኩትን ታሪክ አስታውሳለሁ። ሁለት ወገኖች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በመመስከራቸው ምክንያት ወህኒ ቤት ይገባሉ፡፡

አንደኛው ሰውዬ በጌታ ቤት ውስጥ የእግዚአብሔርን መንገድ እንዴት መሄድ እንዳለበት የብዙ ዘመን መንፈሳዊ ልምድ ያካበተ የዕድሜ ባለፀጋ አዛውንት ነው፡፡ አንደኛው ሰውዬ ደግሞ ወደ ጌታ ቤት ገና በቅርብ ጊዜ የመጣና የእግዚአብሔርን መንገድ እንዴት መሄድ እንዳለበት እምብዛም ልምድ የሌለው ወጣት ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ ሁለቱም ሠዎች የክርስቶስን ወንጌልን በአደባባይ ሲመሰክሩ ይያዙና እስር ቤት ውስጥ ይጣላሉ፡፡

አንድ ዕለት የፍርዳቸው ቀን ሆነ፡፡ ፍርዳቸውም በጋለ እቶን ውስጥ መጣል ነበር፡፡ ፍርዳቸው ከመፈጸሙ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ወጣቱ ልጅ በታሰረበት ጨለማ ቤት ውስጥ ሆኖ ሻማ ለመለኮስ ክብሪት ሲጭር የእጁን ጣት በእሳት ያቃጥላል፡፡ የክብሪቱ እሳት የዋዛ አልነበረም፡፡ እጁን በኃይል ለበለበው። በዛን ጊዜ አጠገቡ ለተቀመጠው ክርስቲያን አዛውንት «እንዴ ይህች የክብሪት እሳት ጣቴን እንደዚህ ከለበለበቺኝ … ነገማ በእቶን እሳት ውስጥ ስጣል ሙሉ አካሌ እንዴት እንደሚቃጠል አስበኸዋል? ስለዚህ ስለ እምነቴ ስል ራሴን ለእቶን እሳት አሳልፌ አልሰጥም» አለ። አዛውንቱም የወጣቱን እምነት መረበሽ አይቶ እንዲህ ሲል መለሰለት፤ «እግዚአብሔር በዚህ እስር ቤት ውስጥ መስዋእት እንድታደርግለት የፈለገው ጣትህን ሳይሆን ሙሉ ሰውነትህን ነው፡፡

ጣትህ ሲቃጠል የሚያግዝህን ፀጋ አልሰጠህም፡፡ ዳሩ ግን ሙሉ ሰውነትህ በእሳት ውስጥ መስዋእት እንዲሆን የሚረዳህን ፀጋ ነገ በሰዓቱ እንደሚሰጥህ አረጋግጥልሃለሁ» ሲል መለሰለት፡፡

አያችሁ አዛውንቱ ለረጅም ዘመን ከእግዚአብሔር ጋር ከነበረው ቁርኝት የተነሳ ሊመጣ ያለው ቀን በራሱ የራሱን ፀጋ ይዞ እንደሚመጣ ያውቃል፡፡ አዛወንቱ ከረጅም የህይወት ልምዱ እግዚአብሔር አምላክ በየዕለቱ ለባሪያዎቹ ያዘጋጀው ፀጋ እንዳለ ያውቃል፡፡ ነገም በራሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይዞት የሚመጣ ፀጋ እንዳለው ያምናል። ወጣቱ ክርስቲያን ልጅ ግን የነገውን እምነቱን መሰረት ያደረገው ከዛሬ ቅንጣት ልምዱ ላይ በመነሳት እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡

ከዚህ ታሪክ እምነት በምክንያት ድርደራ ላይ የተመሰረተ እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡ እምነት ነገ ስለሚሆነው ጉዳይ ሀሳብን እያወጣ አያወርድም። እምነት እግዚአብሔር አምላክ የነገውን መና እንደሚያወርድ አስቦ ዛሬን በእረፍት መንፈስ ይመላለሳል፡፡ ወገኖቼ በዚህ ምእራፍ ማገባደጃ ላይ ስላለፈው ትላንትናና ስለሚመጣው ነገ እያሰባችሁ እንዳትጨናነቁ አሁንም በአጽንኦት አሳስባችኋለሁ፡፡

አንድ መጽሐፍ ላይ ይህንን ጽሑፍ አንብቢያለሁ ፤ «ትላንትና ልክ እንደ ተሰረዘ የገንዘብ ቼክ ነው! ነገ ደግሞ ዛሬ ገንዘብ የሌለው ደረቅ ቼክ ነው! አሁን የምትመነዝረው ቼክህ ቢኖር የዛሬ ቀን ነው! በማስተዋል ተጠቀምበት»፡፡

# 5

## ቢሆን ኖሮ

ሐዋሪያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሠዎች በላከው መልእክቱ «ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ» ሲል ይናገራል (3፡13) ፡ በሀሳባችን ካልሆነ በስተቀር እንዴት ባለፈ ነገር ላይ ተንጠልጥለን እንኖራለን? አዎ በእርግጥ ወደ አለፈው ነገር በሀሳባችን እንነጉድ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ያለፈው ዘመን ትውስታችን ዛሬን ለመኖር ኃይል ሆኖ እንደሚያገለግለን አምናለሁ፡፡

ከዚህ ቀደም ታደርጓቸው የነበሩትን ስዕተቶች አሁንም ደጋግማችሁ በመፈጸም ላይ ናችሁ? ከዚህ የተነሳ እነዚህ ጥያቄዎች በልባችሁ ደጋግማችሁ ራሳችሁን እየጠየቃችሁ ይሆናል ፤ «ለምን እንደዛ አደረግሁ?» ወይም « እንደዚህና እንደዚያ ባደርግሁ ኖሮ» እያላችሁ ይሆናል፡፡ ወገኖቼ «ቢሆን ኖሮ» ከሚል ቃል አጥብቃችሁ ልትጠነቀቁ ይገባል፡፡

ምናልባት ከዚህ ቀደም ያደርጋችኋቸው ነገሮች ሁሉ የግድ መደረግ ስለነበረባቸው ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ውጤታቸውን መራራ ሆኖ አገኛችሁት፡፡ ከዚህ የተነሳ ፊታችሁን ወደ አምላካችሁ አንስታችሁ «እነዚህ ሁሉ ነገሮች ስለምን ወደተፈለገው ነገር አልተለወጡም? ለምን? እግዚአብሔር ሆይ ለምን? ለምን እንደዛ አልሆኑም?» ፈጽሞ ሊገባኝ አልቻለም!

ምክንያቱን ማወቅ አለብኝ! ምክንያቱን እሳካውቅ ድረስ ልቤ አርፎ መቀመጥ አይችልም! ወዮ! አለበለዚያ ይሄ ነገር እረፍት አይሰጠኝም!»

አሁን ያላችሁበት ሁኔታ በዚህ ድምፀት ውስጥ የወደቀ ይሆን?ወይስ በዚህ ጥያቄዬ አሰልችቿያችሁ ይሆን? ያም ሆነ ይህ ራሳችሁን በስቃይ ውስጥ እያስገባችሁ ነው! የራሴም ህይወት ለዘመናት በእነዚህ ጥያቄዎች የተሞላ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ምላሹን ለማግኘት ውጤታማ አልነበርሁም፡፡ ይገርማችኋል እስካዛሬ ድረስ ይህ ነው የሚባል መልስ ያላገኘሁባቸው በርካታ ጥያቄዎችን ወደ ኋላ ጥዬ ዛሬን ደርሺያለሁ፡፡

ከዛ ይልቅ ቅድም በመግቢያችን ላይ እንዳነሳሁት የሐዋሪያው ጳውሎስ ንግግር በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ መዘርጋት እንዳለበኝ ጌታ ተናገረኝ፡፡ ከዚህ የተነሳ በአሁኑ ሠዓት በህይወቴ ወደር የሌለውን የእግዚአብሔርን ሠላም እያጣጣምሁ አለው፡፡

የእግዚአብሔር ቃል በኢሳያስ 26፡3 ላይ «በአንተ ታምናለችና በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ» ሲል ይናገራል። ቃሉን በሚገባ ስናጤነው «በአንድ ጉዳይ ላይ ምላሽ ለማግኘት አይህምሮውን በሚያጨናንቅ ሙሉ ሰላምህ ያገኘዋል» አይልም፡፡ የእውነተኛ የልብ ሰላም ሚስጥር ህያው እግዚአብሔር ላይ ሙሉ በሙሉ ሀሳብን መጣል ነው፡፡

በህይወት ዘመናችን ደስ የማይሉ አያሌ የህይወት ገጠመኖች ተፈራርቀውብናል፡፡ የራሴን ህይወት እንደምሳሌ ባነሳ እልቆ መሳፍርት የሌላቸው ልዩ ልዩ አሳዛኝ የህይወት ገጠመኞች ውስጥ አልፌያለሁ፡፡ እንደውም የአንዳንዶቹ ትዝታ በቀላሉ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ከልቤ ላይ ተፍቆ የሚጠፋ አልነበረም፡፡ ከልቤ ላይ በርሮ እስኪጠፋ ድረስ በርካታ ዓመታትን ፈጅቶብኛል፡፡

ለምሳሌ ከብዙዎቹ የህይወት ተግዳሮቶቼ መካከል አንዱን አስታውሼ ልንገራችሁ፡፡ በትከሻዬ ላይ ህመሙ ጽኑ የሆነ ስብራት ነበረብኝ፡፡ ከዚህ የተነሳ ስለምን ይህ ህመም በእኔ ላይ ሆነ ብዬ ለብዙ ዓመታት በከባድ ምሬትና ሀዘን ውስን ነበርሁ፡፡ ህመሙ ስለምን በእኔ ላይ ተፈጠረ ብዬ በራሴ መንፈሳዊ አተያይ ምክንያቱን ለማግኘት ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን በጭንቅላቴ ውስጥ ሳወጣና ሳወርድ ነበር፤«ለምን እግዚአብሔር አይረዳኝም? ወይም ለምን መፍትሔው ያላቸው ሠዎች መፍትሔውን አይነግሩኝም?» እያልሁ ብዙ ዓመታትን የትከሻዬን ህመም ይዤ ቆየሁ፡፡

በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር አምላኬ ረዳኝ፡፡ ለካ ራሴን በእነዚህ ጥያቄዎች ምክንያት ሌላ መከራ ውስጥ እየከተትሁ ነበር፡፡ ውብ የሆነውን ዛሬዬን ለትላንትናዬ እንቆቅልሽ መልስ አገኛለሁ እያልሁ ከንቱ እያደረግሁት ነበር፡፡

አንድ ቀን እግዚአብሔር «ልጄ ጆይስ አሁን ምርጫው የአንቺ ነው! ወይ ምስኪን ወይም ብርቱ መሆን» አለኝ፡፡

አንዳንድ ጊዜ የትላንትናችሁ ድል ሀሳባችሁን ቆንጥጦ ይዛችሁና እርሱኑ በሀሳባችሁ ስታወጡና ስታወርዱ ዘመናችሁን ታቃጥላላችሁ። የትላንትናችሁ የድል ሚስጥር ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለማወቅ በርካታ ምክንያቶችን በፊታችሁ ትደረድራላችሁ፡፡ ከዚህ የተነሳ በትላንትናው የድል ሚስጥራችሁ ዛሬም ባለ ብዙ የሚያደርጋችሁ ይመስላችኋል፡፡ እኔ ራሴ በዚህ የሆነ ዘመን ላይ በእንደዚህ ዓይነቱ የአስተሳሰብ ችግር እንደበርሁ አስታውሳለሁ፡፡

ይገርማችኋል እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ነጋችሁን በድል እንዳትሄዱበት በራሱ ወጥመድ ነው፡፡ ያለፈው ጊዜ የድል ሆነ የሽንፈት ዳግም ላይመጣ አንድ ጊዜ አልፏል፡፡ ወገኖቼ ሆይ የሚያዋጣችሁ ዛሬን በድል መኖር ነው!

የትላንትናን ድል ማሰብ በራሱ ክፋት የለውም፡፡ እንደውም ትዝታው ደስ ይላል፡፡ ይሁን እንጂ በትላንትና የድል ትዝታ ላይ ብቻ ተደላድሎ መቀመጥ ትልቅ ሽንፈት ነው፡፡ እባካችሁን የትላንትናውን የድል ትዝታችሁን ወደ እግራችሁ ጣሉትና እግዚአብሔር በቀጣይ ዘመን ለእናንተ ወዳዘጋጀቸው የድል ህይወት ዝመቱ! ሐዋሪያው ጳውሎስ በቅዱስ ቃሉ «በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ» ብሎ እንደተናገረ፡፡

«ቢሆን ኖሮ» በሚለው አስተሳሰባችሁ ላይ አሁንም ጥንቃቄ እንድታደርጉ አጽንኦት ሰጥቼ አሳስባችኋለሁ፡፡ ክፉም ሆነ መልካም ነገር በህይወታችሁ ሲሆን «ቢሆን ኖሮ» የሚለው ቃል ከፊት ለፊታችሁ ሊመጣ ላለው ድል እምብዛም አይጠቅምም፡፡ ያለፈውን ዘመን ፈጽሞ እርሱትና ከፊት ለፊታችሁ ያለውን ዘመን በድል ለማለፍ ቁርጠኛ መንፈስን ያዙ!

# 6

## እንደዛ ቢሆንስ?

የሰው ልጆች ግራ እንዲጋቡ ወደ አይህምሮ የሚላክ የጦርነት ቀስት አለ፡፡ በኤፌሶን 6፡16 ላይ «በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ» ተብሎ በተገለጸው ቃል ላይ ይህ ቀስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስያሜ አለው፡፡ ስያሜውም «ፍላጻ» ይባላል፡፡ ጠላታችሁ ሰይጣን ብዙ ጊዜ ፍርሃት በሚፈጥር ንግግር ፍላጻውን ወደ እናንተ ይልካል፡፡ አንዳች ክፉ ነገር በእናንተ ላይ ሊሆን ብሎ! ቢሆንስ?

ገንዘብ ባታገኙስ? ጉዳት ቢደርስባችሁስ? ብትታመሙስ? ከስራ ብትባረሩስ? በህይወት ዘመናችሁ ብቸኛ ብትሆኑስ?እግዚአብሔር ድምጹን ቢነፍጋችሁስ?በሆነ የህይወት አጋጣሚ ውስጥ በሃጢያት ብትወደቅስ?የሆነ ሥራ ሰርታችሁ የሰው መሳቂያ ብትሆኑስ?በማህበራዊ ህይወታችሁ ውስጥ ጥላቻ ቢደርስባችሁስ? … ይቀጥላል፤ በርካታ ሌሎች በምን አልባት ላይ የተመሰረቱ ሌሎች ውድቀቶች ቢደርስባችሁስ?

«ቢሆንሶች» ዝርዝራቸው ተቆጥሮ አያልቅም፡፡ ሰይጣን በዚህ መንገድ ፍላጻውን ወደ ሰው ልጆች አይህምሮ እየላከ፣ የሰው ልጆች ደግሞ በተራቸው ለእነዚህ ቢሆንሶች ምክንያት እየደረደሩ፣ መጠኑ ከፍተኛ ወደ ሆነ የግራ መጋባት ስሜት ውስጥ ይገባሉ፡፡

«ቢሆንስ» የሚለው የሰይጣን ፍላጻን ተከትለው በአይህምሮ ውስጥ የሚፈጠሩ ጨለምተኛ አስተሳሰቦች አሉ፡፡ የ«ቢሆንስ» ፍላጻ ፍርሃት ወለድ ሀሳቦችን እየወለደ ስለ ነጋችን አጥብቀን በፍርሃት እንድንዋጥና እንድንጨነቅ ይጎተጉተናል፡፡

የ«ቢሆንስ ፍላጻ» ከዚህ ምእራፍ በፊት ያነሳነውን የ «ቢሆን ኖሮ» ጥያቄንም ያስከትልብናል፡፡ ሁለቱ ፍላጻዎች ደግሞ በአንድ ላይ በአይህምሯችን ውስጥ ተቀምጠው እንክብካቤ እንድናደርግላቸው ዘንድ ያስገድዱናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ቋንቋ ሁለቱንም ፍላጻዎች ተቋቁመን እንድናፈርሳቸው እንዲህ ሲል ይመክረናል፡፡

የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን (2ኛ ቆሮ 10፡5)

እየተናገርሁ ያለሁትን ሀሳብ ግልጽ በሆነ ምሳሌ እስቲ ልንገራችሁ። የሆነ ዘመን ላይ አገልግሎታችን ሳምንታዊ ስብሰባዎችን የሚያደርግበት ህንጻ አስፈልጎት ነበር፡፡ ከዚህ በፊት ለአንድ ለአምስት ዓመታት ያህል እናገለግልበት የነበረው ህንጻ በእርጅና ምክንያት ወደ መፍረሱ ዋዜማ ተቃርቦ ነበር፡፡ ስለዚህ በዛ ምትክ ለአገልግሎታችን ቢሮ፣ ለስብሰባዎቻችን፣ ለህጻናት መዋያና ፕሮግራሞቻችንን ለሚካፈሉ ሠዎች 300 መኪናዎችን ለማቆም የሚበቃ ሥፍራ ፈለግን፡፡

ባለንበት ከተማ ውስጥ እንዲህ ያለውን ሥፍራ ለማግኘት ምናልባት ቀላል ሊመስል ይችላል፡፡ የሚገርማችሁ ጉዳይ ይህን ሥፍራ በቀላሉ ማግኘት አልቻልንም፡፡ ቢያንስ በትንሹ ሁለት ዓመታትን ፈጅቶብናል፡፡ ከምታስቡት በላይ ተስፋ እስከንቆርጥ ድረስ እጅግ አደከመን፡፡

በዚህ ተግዳሮት ውስጥ እያለን ሰይጣን « አሁንም ባይሆንስ? ህንጻውን ስትፈልጉ ሁለት ዓመት ፈጅቶባችኋል፤ አሁንም ድረስ ህንጻ አላገኛችሁም» የሚል ፍላጻ ወደ አይህምሯችን እየደጋገመ ይልክብን ጀመር፡፡ ሰይጣን በዚህ ብቻ አላበቃም «እንዲህና እንዲያ ያሉትን ንብረቶች ርካሽ በሆነቡት ዘመን ገዝታችሁ ቢሆን ኖሮ አሁን ያላችሁበት ጭንቀት ውስጥ አትገቡም ነበር» የሚል ሌላ ተጨማሪ ፍላጻ ይልክብን ጀመር፡፡ የሚገርመው ነገር ከሰይጣን የሚላኩት ፍላጻዎች ሌሎች በርካታ ጥያቄዎችን እያከታተሉብን ወደ አይህምሯችን መጉረፋቸውን አላቆሙም፤ «የእግዚአብሔርን ፍቃድ ምን እንደሆነ ሳታውቁ ቀርታችሁ ቢሆንስ ? ህንጻን በንብረትነት ለመያዝ ሌሎች አማራጮችን ማወቅ ተስኗችሁ ቢሆንስ ? ህንጻውን በንብረትነት ከያዛችሁ በኋላ ደግሞ የህጋዊ ፍቃዱን ጉዳይ ምንታደርጉታላችሁ ? ህንጻውን አግኝታችሁ ውድ ዋጋ ከፍላችሁ ኋላ ደግሞ በጣም በወረደ ዋጋ ተመሳሳይ ህንጻ ብታገኙስ?»

እግዚአብሔር አምላኬን የማመሰግነው ህንጻን ወደ መያዝ ሀሳብ ከመግባታችን በፊት በግሌ ሰይጣን ወደ አይህምሮዬ ከሚልካቸው ፍላጻዎች እንዴት ነጻ መውጣት እንዳለበኝ ትልቅ መንፈሳዊ ግንዛቤ አግኝቼ ነበር፡፡

ጌታ አስቀድሞ ይህን መረዳት ባይሰጠኝ ኖሮ ያን ጊዜ ራሴን በብዙ ስቃይ ውስጥ ጠላልፌ ባስገባሁ ነበር፡፡ ለማደርጋቸው እያንዳንዱ ውሳኔዎቼ ብዙ ምክንያቶችን እየደረደርሁ ለከፍተኛ ጭንቀት በተዳረግሁ ነበር፡፡

አሁን እንደ ድሮ አስተሳሰቤ አይደለሁም፡፡ ሁሉም ነገሮች በእግዚአብሔር ሥርዓት እንደተቃኙ አምኛለሁ፡፡ በመዝሙር መጽሐፍ «የሰው አካሄድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይጸናል፥ መንገዱንም ይወድዳል» ተብሎ እንደተጻፈ ማለት ነው፡፡

ወደ እግዚአብሔር እየፀለይን በእርሱ ፍቃድ ላይ ብቻ እምነታችንን እናደርጋለን፡፡ ስለዚህ እርሱም ወደ ትክክለኛው ፍቃዱ በትክክለኛው ጊዜ ያደርሰናል፡፡ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር አይዘገይም፤ አይቸኩልምም፡፡ ከዚህ በፊት በህይወታችን በራሳችን መንገድ ነገሮችን ወደ ፍጻሜ ለማምጣት ሞክረናል፡፡ የሚገርመው ነገር የቱንም ያህል ለመፍጨርጨር ብንሞክርም የራሳችን አካሄድ አንዱም ሊረባን እንዳልቻለ ዛሬ ትልቅ ማስተዋል ውስጥ ገብተናል፡፡ የሚገርመው ነገር እግዚአብሔር አምላክ በራሱ ጊዜ፣ ያ ያስጨነቀንን የህንጻ ኪራይ ጉዳይ ወደ ፍጻሜው አምጥቶታል፡፡ እናምናለን በዚህ መንገድ ነገም ጉዳዮቻችንን በራሱ ጊዜ ወደ ፍጻሜ ያመጣልናል!

አሁን ልዩ ልዩ ጉዳዮቻችን እኛ ባሰብንላቸው ጊዜ ስለምን ውጤታማ እንደማይሆኑ ገብቶኛል፡፡ በጊዜው እንዲሆን ያደረኩት ትጋት በሙሉ ጉዳይ በሙሉ ከንቱ ሆኖ የሚቀር መስሎኝ ነበር፡፡ በእርግጥም ያለ እግዚአብሔር ጊዜ በራሳችን ጥረት ብቻ ምንም ነገር ሆኖ መታየት አይችልም፡፡

በእርግጥ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር ያውቃል፡፡ ነገሮች ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ናቸውና፡፡ የማደርገውን ነገር ባላውቅም አሁና ዘና ብዬ ሳልጨናነቅ መኖርን አውቄበታለሁ፡ ፡ ምክንያቱም የሚያደርገውን ነገር የሚያውቀውን አምላኬን አውቀዋለውና፡፡

ወገኖቼ እናንተስ? ኢየሱስን ታውቁታላችሁ? እርሱ ሁሉን አዋቂ፣ በአንድ ጊዜ በሁሉ ሥፍራ የሚገኝ፣ በኃይሉ ፍጹም፣ ሁሉን የሚረዳ፣ በእውቀቱ የሚተካከለው የሌለ አምላክ ነው፡፡

እስቲ ራሳችሁን ዘና አድርጉ! በምክንያቶቻችሁ ላይ ምክንያቶችን ብትደረድሩ ምን ታመጣላችሁ?ከምክንያቶቻችሁ በላይ አምላካችሁ እግዚአብሔር በራሱ ለየት ባለ መንገዱ ሊያስደንቃችሁ አይቻለውምን?

እነግራችኋለሁ እስከ ዛሬ ድረስ ለነገሮቻችሁ ምላሽ ታገኙ ዘንድ  ጥያቄዎችን በጥያቄቻችሁ ላይ እየደረደራችሁ የሄዳችሁበት ጊዚያችሁን እያቃጠለ ግራ መጋባትንና ጭንቆትን አመጣባችሁ እንጂ ምንም የረባችሁ ነገር የለም፡፡

ሀሳቤን በዚህ ላይ ልቋጭ፡-በእናንተ ላይ በእርግጥም እግዚአብሔር እግዚአብሔር ሆኖ ፍጹም በእርጋታ መንፈስ መኖር ብትጀምሩ ምን ይመስላችኋል?

# 7

## በጭንቅላት አትምሩ

ጥልቅ የመንፈስን አለም የመረዳት ፀጋ ይኖረኝ ዘንድ ለብዙ ጊዜ እፀልይ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፤ «ጆይስ አንቺ የመንፈስ አለም የምትረጂበት ፀጋ ማግኘት አትቺይም፡፡ ከዛ በፊት በአይህምሮሽ ለነገሮች ሁሉ ምክንያትን መደርደር ማቆም አለብሽ» አለኝ፡፡

በ1ኛ ቆሮ 2፡14-16 ላይ፡-«ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም» ሲል ይናገራል፡፡ ከዚህ ክፍል እንደምንማረው ተፈጥሮአዊው አለም መንፈሳዊውን አለም ፈጽሞ መረዳት አይችልም። እግዚአብሔር በዚህ ቃል አማካኝነት የተናገረኝን ቃል አጽንቶ ወደ መረዳት እንድመጣ አደረገኝ፡፡ ለነገሮች ጥልቅ መንፈሳዊ ግንዛቤ አገኝ ዘንድ በአይህምሮና በመንፈስ ጣምራነት መንፈሳዊውን አለም አውቄ መናፍስትን በመለየት ፀጋ ማደግ አልቻልም፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንዳየነው «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት» ነውና፡፡ ወገኖቼ አስተውሉ! መንፈሳዊው አለም ተፈጥሮአዊ በሆነው ማንነት ፈጽሞ መረዳት አይቻልም፡፡

በጌታ ኢየሱስ የዳናችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆናችሁ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በእናንተ ውስጥ አድሯል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳችሁ በየጊዜው የተለያዩ ሀሳቦችን እንደሚነግራችሁ አምናለሁ ፡፡

ዳሩ ግን የእናንተ የነፍስ ኃይል ለነገሮች ሁሉ ምክንያቶችን ስለሚደረድር እግዚአብሔር ለእናንተ ያለውን ወቅታዊ ሀሳብ ማወቅ ተስኗችኋል፡፡

እስቲ አንድ የማታውሰውን የራሴን መንፈሳዊ ልምምድ ልንገራችሁ። አንድ ማለዳ «ህይወት በቃሉ ውስጥ» ለሚለው ሳምንታዊ ፕሮግራማችን ለመዘጋጀት ልብሴን እየለባበስሁ ነበር።

ይገርማችኋል! ልብሴን እየለባበስሁ ሳለ በእኛ አገልግሎት መሳካት ትልቅ ሚና ያላትን ታማኝ አገልጋይ እህት ማሰብ ጀመርሁ፡፡ ስለ እርሷ እያሰብሁ ሳለ በድንገት አንድ ሀሳብ መጣልኝ፡፡ በልቤም ለዚህች እህት አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ አሰብሁ፡፡

ከዛም ጌታን «ለእህታችን ሩት ምን ላድርግላት?» ብዬ ጠየቅሁት። ወዲያው የሚገርም ጠንካራ ሀሳብ በልቤ ውስጥ አደረ፡፡ በልብስ መስቀያ ሳጥኔ ውስጥ ከተደረደሩት ቀሚሶች

መካከል ቀዩን ቀሚስ አውጥቼ እንድሰጣት ልቤ አጥብቆ ፈለገ፡፡ ይህን ቀሚስ ከገዛሁት ገና ሦስት ወሩ ነው፡፡ የሚገርመው ነገር ቀሚሱን ገዝቼ በቁም ሳጥኔ ውስጥ ባስቀምጠውም አንድ ቀን እለብሰዋለሁ እያልሁ ቆየሁ።

ከቡቲክ ውስጥ እስከነ ማሸጊያው ገዝቼው አስቀምጬዋለሁ፤ አንድም ቀን ለብሼው አላውቅም፡፡ እህታችን ሩት ከእኔ ይልቅ በቁመትም በመጠንም ተለቅ ትላለች፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ የገዛሁት ልብስ ከእኔ ልኬት በአንድ መጠን ከፍ ያለ ነበር፡፡ ምክንያቱም የዛን ዕለት ቀሚሱን የገዛሁበት የልብስ መደብር ለእኔ መጠን ልክ የሆነ ቀሚስ ስላልነበረው ሌላ አማራጭ አልነበረኝም፡፡ ስለዚህ ቀሚሱን ስለወደድኩት ገዝቼ ወደቤቴ አመጣሁት፡፡ ሌላው ምክንያቴ የቀሚሱ ዲዛይን እጅግ ውብ ስለነበር ለመጠኑ መተለቅ ማንም ሰው ግድ እንደማይለው በማሰቤም ጭምር ነበር፡፡

ወደ ሀሳቤ ልመለስና ይህንን ቀሚስ ለእህታችን ሩት አን ለመስጠት ልቤ እያሰላሰለ ሳለ ጭንቅላቴ ደግሞ «ጌታ ሆይ ልብሱ እኮ አዲስ ነው» ይል ጀመር፡፡ ይኸውላችሁ ጭንቅላቴ ለልቤ ይሰጥ የነበረው ምክንያት ድርደራ እዚህ ግባ የሚባል ምክንያት እንዳልበረ ልብ በሉ! ወዲያም ለጭንቅላቴ እንዲህ ስል በልቤ መለስኩለት «ጭንቅላቴ ሆይ አዲስ ልብስ ለእህታችን ሩት እንዳሰጪ እያልከኝ እንደሆነ እወቅ» አልኩት። በዛን ጊዜ የእግዚአብሔርን የቸርነት ጥግ አስቤ ቢሆን ኖሮ እጅግ ያማረውን አዲስ ልብስ እንጂ አሮጌ የሆነን ልብስ ፈጽሞ ለእህቴ ስጪ እንደማይለኝ አውቃለሁ፡፡

ንጉስ ዳዊት በ2ኛ ሳሙኤል 24፡24 ላይ «እንዲህ አይደለም፥ ነገር ግን በዋጋ ከአንተ እገዛለሁ ለአምላኬም ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ያለ ዋጋ አላቀርብም» ብሎ ኦርናን ለተባለ ሰው ሲናገር እናገኛለን፡፡

ታያላችሁ ሥጋችን ሁልጊዜ የማይረባውን ነገር ለሌሎች ሲሰጥ ሀፍረት አይሰማሁም፡፡ ይሁን እንጂ እኔም ለእህቴ አን አሮጌ የሆነን ነገር መስጠት እንደሌለብኝ በልቤ ጨክኜ ተነሳሁ፡፡ ከልብስ መደብር ታሽጎ እንደገዛሁት ለእህቴ ለሩት አን ለመስጠት ወሰነሁ፡፡

የመጨረሻው ምክንያት ድርደራዬ ደግሞ ትንሽ የሚያስቅ ይመስለኛል፡፡ በሚያሳዝን የለሆሳስ ድምጽ «ጌታ ሆይ ይሄ የሚያምረውን ውድ ቀይ ቀሚስ የገዛሁት እኮ አሁን በጆሮዬ ላይ ካንጠለጠልኩት የብር ጉትቻ ጋር አብሮ ስለሚሄድ ነው» አልኩት፡፡

አይገርምም የጌታን ልብ በሚያሳዝን ድምጽ ኮርኩሬ ሀሳቡን ለማስቀየር ያሰብኩኝ አይመስልም? እግዚአብሔር ግን ሀሳቡን አልቀየርም፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ፀጥ ባለ፣ ኮሽታ በሌለው ድምጹ የጆሮዬንም ጉትቻ ጨምሬ ለእህቴ ለሩት አን እንድሰጣት ነገረኝ፡፡

እግዚአብሔር ከተናገረ ተናገረ ነው፡፡ ከእኛ ጋር ሙግት ውስጥ አይገባም፡፡ ስለ አንድ ጉዳይ በልባችን ፍላጎት በማሳደር ይናገረናል። ድምጹ በልብ ፍላጎት፣ መረዳት በመፍሰስ፣ በመንፈሳችን ላይ ምስልን በመከሰት፣ ለነፍሳችን ድምጽን በማሰማት አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ገሃዳዊ በሆነ የጆሮ ድምጽ ይናገረናል፡፡

ይህንን ልብ አድርጉ እግዚአብሔር ከፍቃዱ ውጪ የሆነ ምንም ነገር አይነግራችሁም፡፡ ፍቃዱም በቅዱስ ቃሉ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ አጋጣሚ የምነግራችሁ ነገር ቢኖር ሁሉም ድምጾች የእግዚአብሔር ድምጾች አይደሉም፡፡ ብዙ ወደ ስዕተት የሚመሩ ድምጾችም እንደሚኖሩ እወቁ። እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ድምጽ የምናውቀው መንፈሱ ለመንፈሳችን በሚሰጠው ምስክርነት ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ለእህቴ ለሩት አን ያንን ቀሚስ መስጠት እንዳለብኝ ተናገረኝ፡፡ ይሁን እንጂ ሥጋዊ አስተሳሰቤ ፈጽሞ እንዳልሰጣት ታገለኝ። ለተናገረኝ ለእግዚአብሔር ብዙ ምክንያቶችን ብደረድርም ከሀሳቤ ጋር ግን አልተስማም፡፡ ማድረግ ያለብኝ ብቻ ተናገረኝ። በመጀመሪያ ላይ ስለ ሩት የነገርኳችሁን ቃል አሁንም አስቡ፡፡ ሩት ለአገልግሎታችን የተሰጠች የእግዚአብሔር ሴት ናት፡፡ በዚህ መሰረት ለሩት አን ምን መስጠት እንዳለብኝ ጌታን ጠየቅሁት፡፡

አይህምሮዬ ምክንያት እየደረደረ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ሊጫነኝ ቢሞክርም በመጨረሻም የአምላኬ ፍቃድ ላይ ፀንቼ ለሩት አን ያንን ውድ ቀይ ቀሚስ መስጠት የመጨረሻ ውሳኔ ማድረግ ነበረብኝ፡፡

የሚገርመው ነገር እግዚአብሔር ያዘዘኝን ትዕዛዝ መፈፀም አልቻኩም፡፡ ብዙዎቻችን የእግዚአብሔርን ፍቃድ ባለመፈፀም በዚህ መልኩ ህይወታችንን እንገፋለን፡፡

ለነገሩ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ማዘግየት በራሱ የለየለት ኃጢያት ነው፡፡ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመስርቶ ድርጊትን መፈፀም ለእግዚአብሔር ታዛዥነት ያሳያል፡፡

እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ ለሩት አን ያንን ቀይ ቀሚስ ሳልሰጣት ሳምንታት ነጎዱ፡፡ እንደውም ሀሳቡ ፈፅሞ ከአይህምሮዬ ጠፋ። እግዚአብሔር ግን አልረሳውም፡፡ ጭራሽ በፀሎት ስፍራዬ «ጌታ ሆይ ሩት አን አገልግሎታችንን እየባረከች ነው፤ እኔስ በምን መንገድ ልባርካት» እያልኩኝ መፀለይ ጀመርኩኝ፡፡ ይገርማል አሁንም ያቺ ቀይ ቀሚስ ይህንን ፀሎት በፀለይኩኝ ቁጥር በድንገት እየመጣች ልቤ ውስጥ ትቀመጣለች። በመጨረሻም «አይ አሁንስ እግዚአብሔር አልታዘዝ እያልኩት ነው» አልኩኝና ልብሲቱን ወሰጄ ለሩት አን አስረከብኩኝ፡፡

ለነገሩ አልገባኝ ብሎ እንጂ ወድጄ የገዛኋትን ልብስ እንደታሸገች በቁም ሳጥኔ ውስጥ ሳለብሳት እንዴት ለሦስት ወር አስቀምጣታለሁ? እግዚአብሔር ለሩት ገዝቶ እንዳስቀመጣት ማገናዘብ ነበረብኝ፡፡ ጌታ አስቀድሞ እኔን ተጠቅሞ ምን ማድረግ እንዳለበት ያውቅ ነበር፡፡ በመግቢያችን ላይ ያየነው «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም» ማለት ይህ ነው (1ኛ ቆሮ 2፡14-16)

ፍጥረታዊው ማንነት «ለምን ጌታ ሆይ? ለምን ? ይላል፡፡ ለምን ይህን ነገር መስዋእት እንዳደርግ ጠየከኝ ?ለምን የጠየከኝ ጉዳይ ቀለል ያለ አይሆንም? ለምን በእኔ ላይ ከበድ ያለ ሆነ ?» ይላል፡፡

ይሁን እንጂ በሮሜ 8፡6 ላይ «ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው » የሚል ቃል ተሰጥቶናል፡፡ ቁጥር 8 ላይ ደግሞ «በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም» ይላል። እግዚአብሔርን ደስ አለማሰኘት ደግሞ የራሳችንም ደስታ ይነጠቃል ማለት ነው፡፡

በዚህ ምእራፍ መጨረሻ የዚህችን መጽሐፍ ዋና ዓላማ እንደገና ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡ «ለምን ጌታ ሆይ? ለምን ?» የሚለው ጥያቄ በህይወታችን ግራ መጋባትን፣ ሰላማችን ሰርቆ በመጨነቅና ሀሴት በማጣት ህይወት ውስጥ እንድንመላለስ ያደርገናል፡፡

ህይወታችሁን በተገቢው መንገድ አጣጥማችሁ መኖር ትፈልጋላችሁ? መልሱ ግልጽና አጭር ነው ፡- ለነገሮቻችሁ ሁሉ በጭንቅላታችሁ  ምክንያትን መደርደርን አቁሙ፡፡

# 8

## «ምክንያት ደርዳሪነት» መታለልን ይፈጥራል

በዚህ ዘመን መታለልን ለማምለጥ ብቸኛው መፍትሔ በሥጋ ሀሳብ ሳይሆን በመንፈስ ምሪት መመላለስ ነው፡፡ ሰይጣን ሁልጊዜ በጭንቅላታቸው ምሪት ብቻ የሚመላለሱ ሥጋዊ ሠዎችን ይፈልጋል። እንደነዚህ ያሉ ሠዎች ከእግዚአብሔር ቃልና ከመንፈሱ ይልቅ ስሜቶቻቸውን ለማዳመጥ ፈጣኖች ናቸው፡፡ አንድን ነገር ማድረግ ሲፈልጉ ለስሜታቸው ቀዳሚውን ሥፍራ ይሰጣሉ፡፡ እኛ ግን ወገኖቼ ለእግዚአብሔር መንግስትና ለራሳችን ደህንነት ስንል በስጋዊ ማንነታችን ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ እንመራ ዘንድ ፍቃዳችንን መስጠት ይገባናል። አይህምሯችን አጋጣሚዎችን ሁሉ እየፈለገ ምቹ መስሎ ያሰበውን በሙሉ በስሜት መነሳሳት ብቻ መከወን ይፈልጋል። መልስ የሌለውን ጥያቄ በፍጹም ማስናተናገድ አይፈልግም፡፡ ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ የስጋን ፍቃድ ወደ መስቀል ላይ ወስዶ ለማኖር ከሚጠቀምበት ዘዴዎች አንዱ የማይመለሱ ጥያቄዎችን ለአይህምሯችን በማቅረብ ነው፡፡ የማይመለሱ ጥያቄዎች በአይህምሯችን ሲፈጠሩ ያለን አማራጭ ወይ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መታመን አሊያም ለጥያቄዎቹ ሥጋዊ ምላሽ ለመስጠት ሌት ከቀን መጨነቅ ነው፡፡

አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ከተቀበለ በኋላ አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ተግባር የዳነውን ሰው ወደ በሳል ክርስቲያንነት መለወጥ ነው፡፡ አንድ ክርስቲያን እርባና ለሌላቸው አይህምሯዊ ጥያቄዎች ግዴለሽ ሆኖ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ ከጣለ ያ ክርስቲያን በሳል ክርስቲያን ነው ብለን መናገር እንችላለን፡፡ ለዚህም ነው እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ያለን እምነታችን እስኪጨምር ድረስ ለጥያቄዎቻችን ሙሉ መልስ የማይሰጠን፡፡ ታውቃላችሁ አይህምሯችሁ ወደ መንፈሳዊ ብስለት እስኪደርስ ድረስ አስተሳሰቡ ሥጋዊ ነው፡፡

በሮሜ 8፡5 ላይ «እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና፥ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ» እያለ ስለ ሥጋዊ አይህምሮና መንፈሳዊ አይህምሮ ሰፊ ትንታኔ ሰጥቷል።

በገላቲያ 5፡17 ላይም «ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም» ይለናል፡፡

እስቲ ተመልሰን በዚህ ምእራፍ መጀመሪያ ላይ ባነሳነው ሀሳብ ዙሪያ ትኩረታችንን እናድርግ፡፡ ተፈጥሮአዊው አይህምሮ እምብዛም ሳይጨናነቅ ሁሉ ነገሩን በአንድ ውስን ሥፍራ ላይ አስቀምጦ በውስን እውቀት ውስጥ እንድንኖር ያደርገናል፡፡

እስቲ ለማገናዘቢያነት የሚረዳችሁን አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡፡ በእኛ የአገልግሎት ቢሮ ውስጥ ልዩ ልዩ ደብዳቤዎችን የምንቀበልበት ረጅም መደርዲያ አለ፡፡ በዚህ መደርደሪያ ላይ የእያንዳንዱ የአገልጋዮቻችንን ስም የተጻፈባቸው በርካታ የደብዳቤ ሳጥኖች አሉ፡፡

ለምሳሌ ለአንደኛው አገልጋይ መልእክት ማስተላለፍ ብፈልግ በአገልጋዩ የደብዳቤ ሳጥን ውስጥ በወረቀት ላይ መልእክቴን አስፍሬ ማስቀመጥ እችላለሁ፡፡

በአንድ ወቅት ግን አንድ ስዕተት ፈጠርኩኝ፡፡ ለአንደኛው አገልጋይ መልእክት ፅፌ በሳጥኑ ውስጥ አስቀመጥኩለት። የሚገርመው ነገር አገልጋዩ ላስተላለፉኩለት መልእክት ፈጣን ምላሽ አልሰጠኝም፡፡ «እንዴ ችግሩ ምንድን ነው?» ብዩ የአገልጋዩን ሳጥን እንደገና ሄጄ ስመለከተው ለካ ደብዳቤውን ያስቀምጡት የእርሱ ባልሆነ የደብዳቤ ሳጥን ውስጥ ነው፡ ፡ ይገርማችኋል አንዳንድ ጊዜ እንደውም ስም ባልተጻፈበት የደብዳቤ ሳጥን ውስጥ በችኮላ መልእክት ያስቀመጥኩበት አጋጣሚ አለ፡፡

እግዚአብሔር በደብዳቤዎቹ ሳጥን አማካኝነት ትልቅ ትምህርት አስተምሮኛል፡፡ ይህ ትምህርት ለእናንተም ይጠቅማል ብዩ አስባለሁ፡፡ ልክ መልእክቶቼን በተሳሳተ የደብዳቤ ሳጥን ውስጥ እንዳስቀመጥኩት እንዲሁ በአይህምሮዬ ውስጥ ልክ ያልሆኑ መልእክቶችንም የማስቀምጥበት አጋጣሚ አለ፡፡ ብዙ ጊዜ ማንኛውንም ነገር ሁሉ በአይህምሮዬ ውስጥ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ፡፡

በዛው ልክ በአይህምሮዬ ውስጥ የምትመላለስ አንድ ያልተበረዘች ሀሳብ ስላለች እግዚአብሔርንም መታመን እፈልጋለሁ። ከዚህም በተጨማሪ በርካታ የምክንያት ድርደራ ሀሳቦች በውስጤ ይመላለሳሉ። እግዚአብሔርንም ደጋግሞ «ምነው እግዚአብሔር ? ምነው ›› እለዋለሁ፡፡

ከዚህ የተነሳ ህይወቴ በብዙ ግራ መጋባትና ሠላም ማጣት ውስጥ ወድቆ አገኘዋለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ራሴን በራሴ የማታልልበት አጋጣሚ አለ፡፡ እግዚአብሔር ረድቶኝ ይህንን ድካሜን በሚገባ ማየት ችያለሁ፡፡

አንዳንድ ጊዜ አውጥቼና አውርጄ  መፍትሔ ያገኘሁለት ሀሳብ እንዳለኝ ይሰማኛል፡፡ ያንን መፍትሔ እንዳለው የተሰማኝን ሀሳብ ይዤ «ውሳኔ ላድርግበት? ወይስ አላድርግበት?›› እያልሁ ብዙ አሰባለሁ፡፡ ይሁን እንጂ በመጨረሻ ብዙ ጥፋቶችን ከፈጸምሁ በኋላ ለካ የፈፀምኩት ስእተት ከበድ ያለ ነው፡፡ ተረዳሁት ያልኩትን መልእክት ያስቀመጥኩት ትክክል ባልሆነ የአይህምሮዬ ክፍል ውስጥ ነው፡፡

እግዚአብሔር አምላክ በምሳሌ 3፡7 ላይ «በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን እግዚአብሔርን ፍራ፥ ከክፋትም ራቅ » ሲል ይመክረናል፡፡ ጌታ በመጨረሻ ላይ ሲያስረዳኝ ልክ እኔ ስለ ራሴ እንዳሰብኩት ብልህ ሰው አልነበርኩም፡፡ እዚህ ጋ ልብ አድርጉ እያልኳችሁ ያልኩት ስለ አይህምሮ የማስተዋል ብቃት አይደለም፡፡ እያልኳችሁ ያለሁት ስለ በራሳችን ዙሪያ ስላለን ግንዛቤ ነው፡፡

በምሳሌ መጽሐፍ ላይ ጠቢቡ ሰለሞን እንዲህ ሲል ይናገራል «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል» (ምሳሌ 3፡5-6)

እግዚአብሔር አምላክ ጉዳያችንን በራሱ መንገድ ግልጽ ሲያደርግልን ምንም ዓይነት ውዥንብርና ግራ መጋባት ውስጥ አንገባም፡፡

ይሁን እንጂ ለጉዳያችን ብዙ ምክንያቶችን መደርደር ስንጀምር ልንወጣበት ወደማንችለው ጭንቀት ውስጥ ፈጥነን እንገባለን። ለዚህም ነው ቅዱስ ቃሉ «በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን እግዚአብሔርን ፍራ፥ ከክፋትም ራቅ» ሲል የሚያሳስበን (ምሳሌ 3፡7)

ይኸውላችሁ ነገሮቻችንን ወደ መፍትሔ ለማምጣት ሁለት መንገዶችን እንጠቀማለን፡፡ አንደኛው መንገድ መንፈሳዊ መንገድ ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ሥጋዊ አስተሳሰብ ያለበት መንገድ ነው። መንፈሳዊው መንገድ ሁልጊዜ ትክክል ነው፡፡ ሥጋዊው መንገድ ደግሞ ስዕተት ብቻ የሞላበት መንገድ ነው፡፡

ይህን ሀሳብ የበለጠ ለማብራራት እስቲ ምሳሌን እንጠቀም፤ አንድ ሰው ወደ እኔ ይመጣና በግሌ አንድ ትንቢት ይነግረኛል፡፡ ወይም ለሊት በእንቅልፌ ተኝቼ አንድ ልረዳው የማይልችለው ህልም አያለው፡፡

በግል ትንቢት ከነገረኝ ሰው የሰማሁትን መልእክትን ወይም ለሊት በእንቅልፍ ላይ ሳለሁ ያየሁትን ህልም ትርጉም ለመረዳት ወደ አባቴ እሄድና «አባቴ ሆይ ትርጉሙን መረዳት አልቻልኩም፤ እባክህን መገለጡን እንድትነግረኝ እጠይቅሃለሁ» እለዋለለው፡፡

ቀጥሎም ያልገባኝን ጥያቄ ወስጄ በመደርደሪያ ላይ እሰቅለዋለው። ከዛ በኋላ ስለዚህ መገለጥ ምንም ዓይነት ጥያቄ ዳግም አላነሳም። ሁሉንም ለእግዚአብሔር እጅ ላይ አሳልፌ እሰጣለሁ፡ እርሱም ጥያቄዬን ሊመልስልኝ

ዝግጁ ከሆነ በመደርደሪያ ላይ ያስቀመጥኩትን ጥያቄ ወስዶ በአይምሮዬ ውስጥ በመንፈሱ አማካኝነት ምላሽ ይኖረው ዘንድ ያደርጋል፡፡ በዮሐንስ 14፡26 ላይ «እግዚአብሔር መታመኛህ ይሆናልና፥ እግርህም እንዳይጠመድ ይጠብቅሃልና» ተብሎ እንደተጻፈ፡፡ ከዚህ በፊት ስለዛ ጥያቄዬ ያልነበረኝን መረዳት መንፈስ ቅዱስ በልዩ መገለጥ አይህምሮዬ ውስጥ የእውቀት መገለጥ እንዳገኝ ያደርገኛል፡፡

ሌላው ስላየሁት ህልም ወይም ስለተነገረኝ ትንቢት ግልጽ መረዳት ይኖረኝ ዘንድ ላደርግ የምችለው የመገለጥ መንገድ አለ፡፡

ይኸውም ያየሁትን ህልም ወይም የተነገረኝን ትንቢት ለተለያዩ ሠዎች መናገርና እነርሱም ያላቸውን መረዳት እንዲያካፍሉኝ ማድረግ ነው። ሁላቸውም ምናልባት የተለያዩ መረዳቶች ሊኖራቸው ይችላል።

ከዚህ የተነሳ ስለ ህልሜና ስለ ሰማሁት ትንቢት ያለኝን እርግጠኛ ያልሆነ የመረዳት ግንዛቤ ይዤ ወደ አንድ ውሳኔ እደርሳለሁ፡፡ ወገኖች ሆይ በእርግጥ ሙሉ ያልሆነውን መረዳቴን ይዤ በዚህ መገለጥ ዙሪያ ሰላም በውስጤ እንደማይሰማኝ በታማኝነት መናገር ያለብኝ አይመስላችሁም? እዚጋ እርግጠኛ ባልሆንኩበት የህልሙ ወይም የትንቢቱ መገለጥ ላይ ጥበብ ያጣ ውሳኔ ውስጥ ለመድረስ መቸኮሌ ወደ ባሰ ግራ መጋባት ውስጥ ይዞኝ እንደሚገባ ልብ በሉ!

አሁንም በድጋሚ አስተውሉ «ምክንያት ደርዳሪነት» ግራ መጋባትን መፍጠሩ አይቀሬ ነው፡፡ ስለ ተለያዩ ጉዳዮች እንዳናስብ አይህምሯችንን እንቆልፈው እያልኳችሁ አይደለም፡፡ ዳሩ ግን በአንድ ጉዳይ ላይ ውጤት ለማየት ለረጅም ጊዜያት በጥሞና ማሰላሰልና ግራ መጋባት ውስጥ ሆናችሁ ምክንያት በመደርደር የምታደርጉት መፍጨርጨር ለየቅል ናቸው፡፡

የግራ መጋባት ስሜት ውስጥ እንደወደቃችሁ ከተሰማችሁ እባካችሁን አንድን ነገር ትክክል ባልሆነ መንገድ እያሰባችሁት እንደሆነ እወቁ!

# 9

## ግራ መጋባት ደስታን ይነጥቃል

በዚህ የመጨረሻ ምእራፍ ውስጥ ግራ የመጋባት ስሜት ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ አጽንኦት ሰጥቼ ልነግራችሁ እወዳለሁ። በ1ኛ ቆሮ 14፡33 ላይ «እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና» የሚል ቃል እናገኛለን፡፡ እንዲሁም በቆላ 3፡15 ላይ «በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ። የምታመሰግኑም ሁኑ » የሚል ተጨማሪ ሀሳብ እናገኛለን፡፡

ግራ መጋባት በቀጥታ የሰላም ተቃራኒ ነው፡፡ «ግራ መጋባት» የሚለው ቃል ከተደበላለቀ፣ ንፁህ ካልሆነ፣ ትርምስምስ ካለ የቃል እሳቤዎች ጋር ተዛማጅነት አለው፡፡ ሰላም የሚለው ቃል ደግሞ ሥርዓትን መጠበቅ፣ አለመረበሽ፣ ውስጣዊ እርካታ ከሚሉ ቃላቶች ጋር በቀጥታ ይዛመዳል፡፡ አንድ ሰው ሰላም ከሌለው በምንም መንገድ ደስተኛ መሆን አይችልም። ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 10፡10 ላይ «ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ» ሲል ተናግሯል፡፡

ከጥቂት ዓመታት በፊት በእግዚአብሔርና በምኖረው ህይወት ፍጹም ደስተኛ የሆነ ህይወት መኖር እንዳለብኝ ወደ ውሳኔ ደረስሁ፡፡ በእርግጥም ኢየሱስ ስለ እኔ ሲል በመስቀል ላይ መስዋእት ከሆነ ያንን ህይወት በሚገባ አጣጥሜ መኖር ያለብኝ እኔ እንደሆንሁ አሰብሁ፡፡

በዮሐንስ 15፥11 ላይ ራሱ ጌታ ኢየሱስ «ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ» ሲል ተናግሯል፡፡

በእርግጥም ኢየሱስ ይህንን ህይወት በሚገባ እንድንኖረው ይፈልጋል፡፡ ግራ መጋባት በመጨረሻም ሊመጣ ካለው የህይወት ግባችን ሊከለክለን ይችላል፡፡

በመጨረሻም ግራ መጋባትና ስቃይ አልባ የሆነ ይልቁንም ፍፁም ደስታ የሞላበትን ህይወት በሚገባ አጣጥማችሁ እንደትኖሩት ላበረታታችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ወገኖቼ ለነገሮቻችሁ ሁሉ ምክንያትን መደርደር አቁማችሁ።

በመንፈሳዊ አለም ብዙ ድል ይዘን ለመጓዝ ሥጋዊ ማንነታችን ወደ ኋላ መጣል ያስፈልገናል፡፡ ምክንያቱም ተፈጥሯዊው አለም ለነገሮች ሁሉ መፍትሔ ለማምጣት ምክንያቶትን ይደረድራልና፡፡ ዳሩ ግን መንፈሳዊው አለም ለነገሮች ምላሽ የሚሰጠው በእግዚአብሔር መገለጥና በእግዚአብሔር ጊዜ ብቻ ነው፡፡

በህይወታችሁ ውስጥ ለነገሮች ሁሉ ምክንያትን መደርደር ካቆማችሁ በእርግጠኝነት እነግራችኋለሁ በሰላማችሁና በደስታችሁ ወደር አይገኝላችሁም!

# አዲስ ህይወትን መለማመድ

ኢየሱስ ክርስቶስን በህይወታችሁ ጌታና አዳኝ እንዲሆን አድርጋችሁ ከዚህ ቀደም ካልተቀበላችሁ አሁን በዚህ አጋጣሚ እርሱን የህይወታችሁ ጌታና አዳኝ አድርጋችሁ እንድትቀበሉ ጥሪዬን አስተላልፍላችኋለሁ፡፡ ፍቃደኞች ከሆናችሁ ከዚህ በታች ያለውን ፀሎት በትክክል እንድትፀልዩ እፈልጋለሁ፡፡

*አባት እግዚአብሔር ሆይ፣ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ የአለም ሁሉ መድሃኒት እንደሆነ አምናለሁ፡፡ እርሱ ስለ እኔ በደልና መተላለፍ ሲል በመስቀል ላይ የእኔን ሃጢያት ተሸክሞ እንደተሰቀለ አምናለሁ፡፡ ስለ እኔ ሲል ወደ ሲኦል ወርዶ ሞትንና መቃብርን ድል አድርጓል፡፡ በአሁኑ ሠዓት ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ በትንሳኤ ሞትን አሸንፎ በአንተ ቀኝ እንደተቀመጠ አምናለሁ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ አሁን እፈልግሃለሁ! ሃጢያቴን ይቅር በለኝ! አድነኝ! በእኔ ህይወት ውስጥ ናና መኖር ጀምር! እንደገና መወለድ እፈልጋለሁ!*

አሁን ጌታ ኢየሱስ በአንተ ልብ ውስጥ እየኖረ እንዳለ በእምነት ተቀበሉ። ኃጢያታችሁ በሙሉ ተሰርዞ በእርሱ አማካኝነት ፀድቃችኋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣም ለዘላለም ከእርሱ ጋር ትሆኑ ዘንድ ወደ ሠማይ መንግስተ ሠማይ ይወስዳችኋል፡፡ ከዚህ በኋላ አንድ የእግዚአብሔርን ቃል የምታስተምርና ቤተክርስቲያን ፈልጋችሁ ክርስቶስን በህይወታችሁ በሙላት መግለጥ ጀምሩ፡፡ ያለ እግዚአብሔር ቃል ምንም ዓይነት ለውጥ በህይወታችሁ አይመጣምና፡፡

# የተወደዳችሁ ሆይ

በዮሐንስ ወንጌል 8፡31-32 ላይ «ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ። እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸሁ » የሚል ክቡር ቃል እናገኛለን፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቃችሁ እንደትይዙ አሳስባችኋለሁ። በልባችሁ ውስጥ ስር ሰዶ እንዲቀመጥ አድርጉት፡፡ ምክንያቱም በዚህ ቃል አማካኝት በ2ኛ ቆሮ 3፡18 ላይ «የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን» ተብሎ ተጽፏልና፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችሁ አድርጋችሁ ስለ መቀበላችሁ ማወቅ ደስ ይለኛል፡ ፡ አካባቢያችሁ ወዳለች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በመሄድ አዲስ ህይወት የምታገኙበትን ጠቃሚ ጽሑፎችንና መረጃዎችን መሰብሰብ ጀምሩ፡፡

በጌታ ፍቅር፤ የእናንተው ጆይስ

# የድነት ፀሎት

እግዚአብሔር ይወዶታል! ከእርሶ ጋር የቅርብ ወዳጅነትን ሊመሰርት ይፈልጋል፡፡ እየሱስ ክርስቶስን የሕይወቶ አዳኝ አድርገው ካልተቀበሉ፥ አሁን ሊቀበሉት ይችላሉ፡፡ ልብዎትን ይክፈቱና ይህንን ፀሎት ይፀልዩ....

“አባት ሆይ! በአንተ ላይ በደልን እንደሰራሁ አውቃለሁ፡፡ እባክህ ይቅር በለኝ፡፡ ኃጢአቴን አንጽተህ እጠበኝ፡፡ በልጅህ በእየሱስ ለመታመን ቃል እገባለሁ፡፡ ልጅህ እንደሞተልኝ አምናለሁ፣ በመስቀል ላይ ስለ እኔ ሲሞት ኃጢአቴን የራሱ አድርጎ ወስዶልኛል፡፡ ከሙታንም እንደተነሣ አምናለሁ። አሁን በዚህ ሰዓት ህይወቴን ለእርሱ አስገዛለሁ።

“አባት ሆይ ስለ ይቅርታና የዘላለም ሕይወት ስጦታህ አመሰግንኃለሁ። ለአንተ ብቻ እንድኖር እባክህ እርዳኝ፡፡ በእየሱስ ስም አሜን !”፡፡

ከልብዎት እንደፀለዩ ሁሉ፥ እግዚአብሔር ተቀብሎዎታል፥ ከኃጢአቶትም አንጽቶታል፥ ከመንፈሳዊ ሞት እስራትም ፈጽሞ ነፃ ወጥተዋል፡፡ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች እያነበቡ ከእግዚአብሔር ጋር በሚያደርጉት የአዲስ ሕይወት ጉዞ ለልቦ እንዲናገርዎት ሁልጊዜ ይፀልዩ፡፡

ዮሐንስ 3፡16 1ቆሮንጦስ 15፡ 3-4

ኤፌሶን 1፡4

ኤፌሶን 2፡ 8-9

1ኛ ዮሐንስ 1፡9

1ኛ ዮሐንስ 4፡ 14-15

1ኛ ዮሐንስ 5፡1

1ኛ ዮሐንስ 5፡ 12-13

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ቤተክርስቲያን እንዲያገኙና ከክርስቶስ ጋር ባለዎት ሕብረት እንዲያድጉና እንዲበረታቱ ይፀልዩ። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከእርስዎ ጋር ነው፡፡ ቀስ በቀስ በየእለቱ ይመራዎታል፡፡ ለእርስዎ ባዘጋጀው የተትረፈረፈ ሂወት እንዴት መኖር እንዳለብዎት ያሳይዎታል፡፡

እህታችን ጆይስ እግዚአብሔር በምድራችን ላይ በሙላት ካሰነሳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች መካከል አንደኛዋ ናት፡፡ ኒዎርክ ታይምስ መጽሔት በአንድ ወቅት መጽሐፎቻቸው ከሚነበቡላቸው ሠዎች መካከል በግምባር ቀደምትነት አስቀጧታል።

ይህቺ የእግዚአብሔር ሴት በአለም አደባባይ ላይ በሥነ ጽሑፍ ትሩፋቶቿ አንቱታን እንድታገኝ ያደረጓት መጽሐፍት መካከል እንሆ ጥቂቶቹን፡- ህይወትን ቀሊል የሚያደርጉ 100 መንገዶች፣

ተስፋ አትቁረጥ፣ ከአህይምሮ ውጊያ ጋር ትንታኔ የሚሰጡ በርካታ የቤተሰብ መጽሐፍት እንዲሁም ፈረንካና በማንኛውም ደቂቃ የተባለሁለት የክርስቲያን ልብወለድ መጽሐፍት የሆኑትን ለአንባቢያን አቅርባለች።

ጆይስ ማየር ከእነዚህ የሥነ ጽሑፍ ትሩፋቶች በተጨማሪ በሺህ የሚቆጠሩ በርካታ

የድምጽና የምስል ቃለ እግዚአብሔር አስተምሮቶቿንም ለመላው አለም እንዳቀረበች ይታወሳል፡፡ ጆይስ ማየር

በመላው አለም በሚሊዮኖች ዘንድ የሚታወቅ የራዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራም አላት፡፡ ይህ ፕሮግራም በየዕለት ህይወታችን እንደሰት የሚል ፕሮግራም ነው፤ በፕሮግራሙ አማካኝነትም ሠዎች በመላው አለም ህይወታችን በደስታ ህይወት ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት ሆኗል፡፡

በዚህ ርእሰ ጉዳይና በሌሎች ርእሶች እህታችን ጆይስ በመላው አለም በሚደረጉ የጅማ ወንጌሎችና ሴሚናሮች ላይ እየተገኘች ታገለግላለች። በአሁኑ ሠዓት እህታችን ጆይስ ከውድ ባለቤቷ ከዴቭ ጋር በቁጥር አራት ከሆኑት ውድ ለጆቻቸው ጋር አሜሪካ ምድር በሚዚዮሪ ግዛት በቅዱስ ሉይስ ከተማ ይኖራሉ፡፡

Joyce Meyer Ministreies

P0.Box 655

Fenton, Mo 63026

USA

(636) 349-0303

www.joycemeyer.org

Joyce Meyer Ministreies –Canada

Lambeth Box 1300

London, ON N6P ITS

Canada

1-800-722-9673

Joyce Meyer Ministreies –Australia

Locked Bag 77

Mansfield Delivery Center

Queensland 4122

Australia

(07) 3349 1200

Joyce Meyer Ministreies –England

P0.Box 1549

Windsor SL4 1GT

United Kingdom

01753831102

Joyce Meyer Ministreies

P0.Box 5

Capetown 8000

South Africa

(27) 21-701-1056

## ጆይስ ማየር ከዚህ ቀደም ያሳተመቻቸው መጽሐፍት

በአዲስ ቀን አዲስ አምልኮ

ደፍሬ ልጠይቅህ

ፈረንካው

የቀላል ፀሎት ኃይል

የዕለት ተዕለት መጽሐፍ ቅዱስ

ጀግናዋ ሴት

በትልቁ ተመልከት በትልቁ ይሰማህ

የአህይምሮ የጦርነት ቀጠና

የአህይምሮ የጦርነት ቀጠና … ለታዳጊዎች

የአህይምሮ የጦርነት ቀጠና … ለህጻናት

የአፅድቁልኝ ሱሰኝነት

ቀንን በድል ማጠናቀቅ

ሃያ አንዱ የሰላምና የደስታ ሚስጥራት

የእግዚአብሔር ቃል በመናገር የሚገኝ የድል ሚስጥር

ደስታህን የሚነጥቁ ሰባቱ ጉዳዮች

ቀንን በድል መጀመር

ውበት ለአመድ (እንደገና ተሻሽሎ የቀረበ)

እግዚአብሔርን እንዴት እንሰማለን

እግዚአብሔርን በቅርበት ማወቅ

የይቅርታ ኃይል

የቁርጠኝነት ኃይል

የመልካም ሀሳቢነት ኃይል

የመንፈሳዊ ኃይል ሚስጥር

የጌታ ጦርነት

ለየት ያለ አኗኗር የኃይል ሚስጥር

ሰይጣንን በእግር ሥር የሚጥሉ ሰባቱ መንገዶች

ታዲጊዎችም ሠዎች ናቸው

በመንፈስ መሞላት

ቀለል ለማለት ዋጋ መስጠት

በጸሎት ውስጥ ያለ ሀሴት

ልባችሁ አይድከም

እግዚአብሔር የፈጠረው ሰው መሆን

በመሰራት ላይ ያለ መሪ

እንደምን አደራችሁ ይህ እግዚአብሔር ነው (የስጦታ መጽሐፍ)

ኢየሱስ - ከስሞች በላይ ያለ ስም

ትዳር እንዲሰምር

(ይህ መጽሐፍ ከዚህ ቀደም «አግብቻለሁ እርዳኝ»

በሚል ርእስ ታትሞ ነበር)

ስለ ፍቅር አሳንሰኝ

በኢየሱስ ስም ተፈወሱ

ራስን በመሆን የሚመጣ ስኬት

ደካማ ተዋጊዎችና ራሳቸውን የሳቱ ቅዱሳን

ስለምንም አትጨነቁ

የቀጥታ ንግግር ስብስቦች

አትፍራ!

ስሜቶቻችንን መቆጣጠር

የተሰበረው ልብ ሲጠገን

እኔና ሰፊው አፌ

ለመበልፀግ ተዘጋጅ

እንዳትፈራ

በድንገት እግዚአብሔር በህይወትህ ሲንቀሳቀስ

ባለህበትና በምትሄድበት የህይወት መንገድ ላይ መደሰት

አዲስ የአኗኗር ዘይቤ

ለምን ጌታ ሆይ?

መቼ ጌታ ሆይ ?

ቃሉ፣ ስሙና ደሙ

እንደምወዳቸው ንገራቸው

ሠላም

ለእግዚአብሔር ፀጋ ካልሆነ

ሰባቱ የደስታ ሌቦች

በዴቭ ሜይር የተጻፈ መጽሐፍ

የህይወት መስመሮች

# ግራ መጋባትን ቻዎ ደስታን ደግሞ ታዲያስ በሉት !



ግራ ተጋብታችኋል? ፍጹም የማታውቁት፣ ግራ ያጋባችሁ አንዳች ነገር ዛሬ በህይወታችሁ እያለፈ ነው? ህይወታችሁ በዚህ መልኩ ለምን እየሄደ እንዳለ ጥያቄ ተፈጥሮባችሁ ይሆን? ከዚህ የተነሳ ራሳችሁን ‹‹ጌታ ሆይ ለምን?›› እየጠየቃችሁ ይሆን? ይገርማችኋል የብዙ መጽሐፍት ደራሲ የሆነቺውን ጆይስ ሜይርንም ሳይቀር በአንድ ወቅት ይህ ጥያቄ ወጥሮ ይዧት ነበር ። ይህ ጥያቄ ጌታ የሰጣትን ሰላምና ደስታን እንዴት እንደነጠቃት እስካወቀቺበት ዕለተ ቀን ድረስ ... ። ዛሬም እንደ እህታችን ጆይስ እናንተም ይህን ጥያቄ መግታት ትችላላችሁ ። እህታችን ጆይስ ሠላምና ደስታዋን እንዴት እንደመለሰች ከህይወት ልምዷ ተነስታ እንዲህ ስትል ትመክረናለች ።

- ለተፈጠሩ ጥያቄዎቻችን በሙሉ መልስ ሰጪ ባሪያ መሆናችንን እናቁም ።
- ግዚአብሔር ላይ ብቻ መደገፍን ተማሩ ።
- ስላለፈው ቀንና ስለሚመጣው ቀን ማሰባችሁን አቁሙ ።
- ለማይመለሱ ጥያቄዎቻችሁ ከአህይምሮ ጋር ትግል ማድረግን ትታችሁ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ምላሽ ማግኘትን ተለማመዱ ።

ወገኖቼ ‹‹ጌታ ሆይ ለምን?›› በሚለው ጥያቄ ተይዛችሁ ከሆነ እግዚአብሔር እየጠየቃችሁት ያለው ጥያቄ ፈጽሞ ትክክል አይደለም ። ይህች መጽሐፍ አንብቧት! በዚህ ዙሪያ አሳማኝ ገለጻዎችን አድርጋለች ። ከዚህ በፊት ገብታችሁበት ወደማታውቁት የደስታ ህይወት ውስጥ ትገባላችሁ !

ጆይስ ማየር አገልግሎት